ይህን ፅሁፍ በማንበብ ለእርስዎ እና ለልጆችዎ ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቤት የመጀሪያዉን እርምጃ ወስደዋል። ቀጣዩ እርምጃ ከተከታዮቹ ድርጅቶች እገዛን መጠየቅ ነዉ፡

<u>**የሀብት ምንጭ - ሪሶርስ፡**</u>

**ብሔራዊ የቤት ውስጥ ረብሻ ቀጥታ መስመር (National Domestic Violence Hotline)**

1-800-799-7233

*የማዳመጥ ችግር ካለብዎ እና እንግሊዘኛ ተናጋሪ ከሆኑ፤ 1-800-787-3224 ይደውሉ።*

**መመሪያዎች፡** እንግሊዝኛ ተናጋሪ ኦፕሬተር ጥሪዎን ይመልሳል። የቋንቋዎንና አገርዎን ስም ይናገሩና ወደ አስተርጓሚ እስኪገናኙ ያልበዛ ደቂቃዎች ይጠብቁ።

**አካባቢያዊ አገልግሎቶች፡**

ይህ በራሪ ፅሁፍ በተከታዮቹ ቋንቋዎች ይገኛል፡ አረብኛ፣ አርሜኒያን፣ ቦስኒያ/ክሮሺያን፣ ካምቦዲያ/ኬመር፣ ቻይኒዝ፣ ዳሪ/ፋርሲ፣ ሞንግ፣ ኩርዲሽ፣ ላኦቲያን፣ ራሺያን፣ ሶማሊ እና ቬትናሚዝ። ለማዘዝ በተከታዩ ይደዉሉ፡ (916) 322-2087 የስደተኞች ጤና ክፍል።

ይህ ብሮሽር የተከለሰው እና የተዘጋጀው በካሊፎርኒያ የጤና አገልግሎቶች ዲፓርትመንት፣ በስደተኞች ጤና ክፍል፣ ከቤት ውስጥ ረብሻ መከላከል ፕሮግራም፣ ከሎስ አንጀለስ የስደተኛ ጤና ሰራተኛ እና ከሜርሰድ ቀበሌ እና የሳንዲያጎ ካቶሊክ ቻሪቲ እገዛ ነው። ኦርጅናል ይዘት በ AYUDA, Inc. እና ቤተሰባዊ ረብሻ መከላከያ ፈንድ (Family Violence Prevention Fund) ተፃፈ። 6/99

# ማንም ሲጎዳዎ መብት የለዉም፤ የሚወዱትም ቢሆን፡



# ለስደተኛ ሴቶች ጥያቄዎች እና መልሶች



**የቤት ውስጥ ረብሻ** ባለቤትዎ፣ የቀድሞ ባለቤትዎ፣ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ (ቤትዎ ውስጥ የሚኖር) አካላዊ ወይም ስሜታዊ ጉዳቶች ቀን በቀን ወይም ሳምንቱን ሙሉ ሲያደርስብዎ ነው። በዩናይትድ ስቴትስ፤ የቤት ውስጥ ረብሻ **"ወንጀል"** ነው። ተከሰተ የሚባለው እሱ፡

- ካስፈራራ እና ጉዳት ካደረሰብዎ።
- ግብረ ስጋ ግኑኙነት ማድረግ ሳይፈልጉ አስገድዶ ካደረገ።
- ዶክተር እንዳያዩ የሚከላከል ከሆነ።
- የቤት ቁሳቁስዎን የሚወድም ከሆነ፣ የቤት እንስሳ የሚገድል ከሆነ፣ የግል የሚወዱትን ንብረት የሚሰብር ከሆነ እና ወዘተ።
- ገንዘብዎ የሚቆጣጠር ከሆነ ፣ ጓደኞችዎን እና ቤተሰብዎን ማየት የሚከለክልዎት ከሆነ።
- ከቤትዎ እንዳይወጡ የማይፈቅድ ከሆነ።

## <u>አደጋ ዉስጥ ካለሁ ምን ማድረግ እችላለሁ?</u>

- ለድንገኝተኛ ጊዜ እገዛ፤ 911 ይደውሉ እና ለኦፕሬተርዋ ምን ቋንቋ እንደሚናገሩ ይንገሩ።
- ወደ **"መጠለያ"** ይሂዱ። **"መጠለያ"** እርስዎና ልጆችዎ ደህንነታችሁ ተጠብቆ የምትተኙበት እና የምትመገቡብት ትልቅ ቤት ነው። መጠለያዎች አብዛኛውን ጊዜ ነፃ እና ብዙውን ጊዜ ደግሞ በማህበረሰብዎ ውስጥ ሌሎች አገልግሎቶችን መረጃ የሚያገኙባቸው ናቸው።
- ወደ ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብ አባል በመሄድ ይቆዩ። የት እንደሚቆዩ ለማንም <u>**አይናገሩ**</u>።
- ወደ አሜሪካ እንዲመጡ ስፖንሰር ለሆነዎ ወኪል ይደዉሉ። የህግ እገዛ ስለማግኘት ይጠይቁ።

ከቤትዎ ከለቀቁ ልጆችዎን ከእርስዎ ጋር ለመዉሰድ የቻሉትን ሁሉ ጥረት ያድርጉ። ከቻሉ ተከታዮቹንም ይዉሰዱ፡

- የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ካርድ።
- I-94 ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ካርድ።
- የባንክ አካዉንት መዛግብት፡ የቼክና የባንክ ደብተሮች።
- የልደት የምስክር ወረቀት፡ የትዳር ማስረጃዎች።
- የዌልፌር ወረቀቶች፤ የሜዲ ካል ወረቀቶች፤ የምግብ ኩፖኖች።
- ሁሉም የስደተኛ ሰንዶች።
- ማህበራዊ ዋስትና ካርድ።
- መድኃኒቶች።

እንዲሁም ገንዘብዎን ሚስጥራዊ በሆነ ቦታ ያስቀምጡ፤ ተጨማሪ ቁልፎችን እና መቀየሪያ ልብሶችንም በዚሁ ሚስጥራዊ ቦታ ያስቀምጡ።

የሰነዶችን ዋና ወይም ቅጅ ማግኘት ካልቻሉ ሰነዶች ላይ ያለ መረጃን ወረቀት ላይ ይፃፉ። እነዚህን እቃዎች ሲወጡ በፍጥነት እንዲያገኟቸዉ በቦርሳ ዉስጥ ያስቀምጧቸዉ። የሰነዶቹን ቅጅዎች በጓደኛዎ ቤትም ማስቀመጥ ይችላሉ።

## <u>ለፖሊስ መደወል አለብኝ?</u>

**አዎ።** የቤት ዉስጥ ረብሻ **"ወንጀል"** ነዉ። ፖሊሱ እርስዎን እና ልጆችዎን ወደ ቤተሰብዎ ወይም የጓደኛዎ ቤት፤ ወይም እንደ መጠለያ ያለ ደህንነትዎ የሚጠበቅበት ቦታ ሊወስድዎ ይችላል። ፖሊሱ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ካመነ፤ ባለቤትዎን ወይም የወንድ ፍቅረኛዎን በቁጥጥር ስር ሊያዉሉ ይችላል። ፖሊስ ኦፊሰሩ የእርስዎን ቋንቋ የማይናገር ከሆነ፤ ከልጅዎ ወይም ከባለቤትዎ ወይም ከወንድ ፍቅረኛዎ ሌላ አንድ ሰው አስተርጓሚ እንዲሆንዎ ይፈልጉ።

የፖሊሲ ኦፊሰሩ የ **"ክስተት ሪፖርት"** እንዲሞላ ሁልጊዜ ይጠይቁ፤ ይህም ምን እንደተከሰተ (ለፖሊሱ ለምን እንደ ደወሉ) ያብራራል። የ **"ክስተት ሪፖርት ቁጥር"** ይጠይቁ፤ የሪፖርቱ ቅጂ እንዲያገኙ። ሪፖርቱን ያደረገውን ፖሊስ ኦፊሰር ባጅ ቁጥር (የፖሊስ ኦፊሰር መለያ ቁጥር) ይጠይቁ እና ይፃፉ።

ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከተወሰደ፤ ወደቤት እንዲሄድ ከሁለት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይለቀቃል። ይህን ጊዜ ደህንነትዎን መጠበቂያ ቦታ ያግኙ።

Amharic Translation Date: May 2015

**ወደፊት ራሴን እንዴት ነው የምጠብቀው?**

**“የጥበቃ ትዕዛዝ”** ለማግኘት ይሞክሩ። የጥበቃ ትዕዛዝ **“የእገዳ ትዕዛዝ” ወይም “ዕቀባ”** ተብሎ ይጠራል። ጥቃት አድራሹ ሰው እርስዎ፣ ልጆችዎ እና ሌላ የቤተሰብ አባላት አጠገብ እንዳይደርስ ማስቆም ይችላል። ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ከቤትዎ እንዲወጣ እና በስደተኛ ጉዳዮችዎ ሁኔታ ላይ ጣልቃ እንዳይገባ መጠየቅ ይችላሉ። የጥበቃ ትዕዛዙ ተፈፃሚነት እንዲኖረው፤ ወደ ፖሊስ በፈቃደኝነት ለመደወል እና ትዕዛዙን ለማክበር ፈቃደኛ ሊሆኑ ይገባል።

**የዩ.ኤስ ዜጋ ባልሆንም እንኳ የጥበቃ ትዕዛዝ ማግኘት እችላለሁ ዜጋ?**

**አዎ።** የጥበቃ ትዕዛዝ ለማግኘት ዜጋ ወይም ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ሊኖርዎት አያስፈልግም። አንድ ጠበቃ ሊያግዝ ይችል ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊ አይደለም። ማመልከቻውን በፍርድ ቤት፣ የሴቶች መጠለያ፣ የህግ አገልግሎቶች ማግኛ ቢሮዎች፣ እና በአንዳንድ ፖሊስ ጣቢያዎች ማግኘት ይችላሉ። በሚኖሩበት አካባቢ ስለ ጥበቃ ትዕዛዙ ፖሊሲ መረጃ በተመለከተ: (1) **“የህግ አገልግሎቶች ጠበቃ”** (ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች ነፃ የህግ አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ጠበቃ)፤ **ወይም** (2) እርስዎን ስፖንሰር ያደረግዎት ኤጀንሲ፤ **ወይም** (3) በአካባቢዎ ያለ የስደተኞች እገዛ ፕሮግራም።

**ያለ ባለቤቴ እርዳታ ህጋዊ ቋሚ መኖሪያ ማግኘት እችላለሁ?**

ቫዮለንስ አጌነስት ውመን አክት (Violence Against Women Act, VAWA) ሰነድ አልባ ለሆኑ የዩ.ኤስ ዜጋ ወይም ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ያለው ሰው አግብተው መኖሪያቸውን ለማግኘት ለሚጥሩ ሴቶች መንገድ ይፈጥራል። የመኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት የስደተኞች እና ዜግነት አገልግሎት (Immigration and Naturalization Service, INS) በባለቤትዎ ከማመልከት ይልቅ፤ ለራስዎ እና ለልጆችዎ በራስዎ ማመልከት ይችላሉ። ይህም **“በራስ ጥያቄ ማቅረብ”** ይባላል። የቤት ውስጥ ረብሻ ለመሆኑ የፖሊስ ሪፖርት ቅጂ እንደ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎ። ባለቤትዎ በሂደቱ ላይ ምንም ሚና አይኖረውም እና የመኖሪያ ማመልከቻ ማስገባትዎንም ማወቅ የለበትም። ህጉ ውስብስብ ነው።

ወደ INS ከመሄድዎ በፊት የመጠለያ ሰራተኛውን ወይም፣ የስደተኛ ጠበቃን፣ ወይም በዚህ ብሮሸር ጀርባ ላይ ከተዘረዘሩት ኤጀንሲዎች አንዱን ያናግሩ። በራስ ጥያቄ ለማቅረብ ያገባ መሆን አለበት። ከባለቤትዎ የፍቺ ጥያቄ ወረቀት ከደረስዎ ወዲያውኑ ጠበቃ ያግኙ።
በINS ቁጥጥር ስር ከዋሉ እና “ይወገድ እርምጃ” ውስጥ ከሆኑ (ቀደም ብሎ ከሀገር ማባረር ይባላል ነበር)፤ ለመለቀቅ የማመልከት እድል ሊኖርዎት ይችላል። የቤት ውስጥ ረብሻ ለመሆኑ የፖሊስ ሪፖርት ቅጂ እንደ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎ።

**ባለቤቴ ትቼው የምሄድ ከሆነ ልጆቼን ይዞብኝ እንደሚሄድ እያስፈራራኝ ነው። ምን ማድረግ እችላለሁ?**

ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ልጆችዎን ወደ ትውልድ ሀገሩ ይዞ ለመሄድ እያስፈራራዎ ከሆነ፤ የሚከተሉትን መስፈርቶች በመከተል እርዳታ ያግኙ:

1. “የማሳደጊያ ትዕዛዝ” ያግኙ (ልጆችዎን ራስዎ ጋር ለማስቀረት የሚረዳዎትን ህጋዊ ሰነድ)። ትዕዛዙ ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ልጆቹን ከዩ.ኤስ ከመውሰድ ሊያስቆመው ይችላል።

2. ልጆቹን የማሳደግ ቪዛ ወይም ፓስፖርት ከማግኘት እንዲቆም የማሳደጊያ ቅጂዎን ለዩ.ኤስ የስቴት ዲፓርትመንት ይላኩ። የባለቤትዎን ወይም የወንድ ፍቅረኛዎን የትውልድ ሀገር ለዩ.ኤስ ኤምባሲ ቅጂውን ይላኩ።

3. የትዕዛዙን ቅጂ ለልጆችዎ ትምህርት ቤቶች ይስጡ። ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ልጆችዎን ከእርስዎ ውጪ ለማንም ለቀው እንዳይሰጡ ይንገሩ።

**ባለቤቴን ከተውኩት ልጆቼን እና እኔን በገንዘብ መደገፍ (መጠበቅ) የምችለው እንዴት ነው?**

የልጆችዎ አባት ያሉበት የስደተኝነት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በገንዘብ እንዲደግፍ ህጉ ይጠይቃል። ይህም አብራችሁ ባትኖሩ እንኳን እና እስከመጨረሻውም ባትጋቡ ተግባራዊ ይሆናል።



በካሊፎርኒያ የልጅ ድጋፍ ለማግኘት የስደተኛ ጠበቃ ወይም ስፖንሰር ያደረግዎትን ኤጀንሲ ያግኙ። አንዳንድ ያገቡ ሴቶች ከባላቸው ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፊ ለማግኘት ብቁ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። ስደተኛ ሴቶች የ I-94 ካርዳቸውን በመጠቀም ለመስራት ብቁ መሆናቸውን ለማሳየት ማረጋገጥ ይችላሉ።

**ስደተኛ ነኝ። ዌልፌር እና ሜዲካል ለመቀበል ህጋዊ መብት አለኝ?**

**አዎ።** ዩናይትድ ስቴትስ እንደመጡ በመጀመሪያዎቹ አምስት (5) አመታት ለምግብ ኩፖን (Food Stamps)፤ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ጊዜያዊ እገዛ (Temporary Assistance to Needy Families)፤ ሜዲ ካል (Medi-Cal) እና ሌላ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራም ልክ እንደ ዩ.ኤስ ዜጋ ያገኛሉ። አብዛኛዎቹ አምስት (5) አመት እና ከዛ በላይ የቆዩ ስደተኞች ለምግብ ኩፖን ብቁ ናቸው። ለሜዲ ካል፣ ለምግብ ኩፖን፣ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ጊዜያዊ እገዛ እና አጠቃላይ የስደተኞች እገዛ በዩናትድ ስቴትስ አምስት (5) አመታት እና ከዛ በላይ ለቆዩ ብቁ ሆኖ መገኘት ከግዛት ግዛት ይለያያል። እባክዎ የስደተኛ ጠበቃ ወይም ስፖንሰር ያደረግዎትን ኤጀንሲ ያናግሩ።.

**የዩ.ኤስ ዜግነት ያላቸው ልጆቼ ለመግንስት ጥቅማጥቅሞች እና ሜዲካል ህጋዊ ናቸው?**

**አዎ።** የዩ.ኤስ ዜግነት ያላቸው ልጆችዎ እንደማንኛውም የዩ.ኤስ ዜግነት ያላቸው ልጆች ከመንግስት ህጋዊ ጥቅማጥቅሞች ተጠቃሚ ናቸው።

**ከእነዚህ አንደኛውን እርምጃ ብወስድ ከሀገር እባረራለሁ?**

**አይ፤** በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ **ህጋዊ ሰነዶች ይዘው** ካሉ፤ የቤት ውስጥ ረብሻን ቅሬታ ፋይል በማስደረግዎ ከሀገር አይባረሩም። ወንጀል ከፈፀሙ፣ ወይም የቪዛዎን ሁኔታ ካልተከተሉ፣ ሀሰተኛ ሰነዶች ካልዎት፣ ከሀገር ሊባረሩ ይችላሉ።

**እርምጃ ከወሰድኩ ባለቤቴ ወይም የወንድ ፍቅረኛዬ ከሀገር ይባረራል?**

ከመጠለያ ወይም ከጠበቃ እርዳታ ካገኙ ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ከሀገር ያለመባረር እድላቸው ከፍተኛ ነው።

ወደ ፖሊስ ከደወሉ እና ባለቤትዎ ወይም የወንድ ፍቅረኛዎ ከተያዘ እና በወንጀል ክስ ከተፈረደበት፤ ባለው የስደተኝነት እና የክሱ ሁነት ላይ ተመስርቶ ከሀገር እንዲባረር ሊደረግ ይችላል።

**የራስዎን እና የልጆችዎን ደህንነት ይጠብቁ።**

**ያስታውሱ፤ የቤት ውስጥ ረብሻ ወንጀል ነው።**

**እርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ነው።**

Amharic Translation Date: May 2015